የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ድጋፍ ኮሚቴ ሆላንድ.

**CUDP support committee Holland (CUDP- SCH)**

Contact us: Address P. o box 25763, 2502 HT The Hague, Phone No.  +03120-6916923, +0 3170-4451682, Email kinijit.sch@gmail.com

# የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ድጋፍ ኮሚቴ በሆላንድ የጠራው ሕዝባዊ ስብሰባ የአቋም መግለጫ፦

የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ በሆላንድ አፕሪል 08 ቀን 2006 ዓ ም በአምስተርዳም ከተማ የጠራው የመጀመሪያ ሕዝባዊ ስብሰባ ፣ ቁጥራቸው በርካታ የሆነ ኢትዮጵያዊያን በተገኙበት ተካሄደ።

የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ በሆላንድ ከተመሰረተ ከጥር ወር መጨረሻ 2006 ዓ ም ጀምሮ፣ ባለፉት ጊዚያት ውስጥ ያከናወናቸውንና በቀጣይነት በአጭር፣ በመካከለኛና በረዢም የጊዜ እቅዱ ፣ሊያከናውናቸው ስለአሰባቸው ተግባራት በተመለከተ፣ የእለቱ ጉባዔ ሰብሳቢ አጭር የመግቢያ ንግግርና ገለፃ ካደርጉ በኋል፣ ከአምስት ሠዓት በላይ የፈጀው ፈርጀ ሠፊ ጉባዔ፣ ከብዙ በጥቂቱ ቀጥሎ እንደተዘገበው በተሳካ ሁኔታ ተከናውኗል።

የስብሰባው አወያይ ከነበሩት ሁለት እንግዶች መካከል አንዱ አቶ ጌታቸው አለማየሁ በእንግሊዝ የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴና የአውሮጳ ቢሮ አስተባባሪ ሲሆኑ፣ እሳቸውም፣ ያለፈውን የግንቦት ወር 2005 ዓ ም አገራዊ ምርጫ ጋር በተዛመደ፣ ቅድመ ምርጫ፣ በምርጫውና ከምርጫው በኋላ ስለነበረውና ስለኢህአዴግ እኩይና ፀረ ሕዝብ ተግባር አስመልክተው ባደረጉት ጠለቅ ያለ ትምሕርት ሰጪ ገለፃ፣ በተሰብሳቢው ሕዝብ ዘንድ በከፍተኛ ተመስጦና በአንክሮ ተደምጧል።

በመቀጠልም ዶ/ር አሰፋ ነጋሽ የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ በሆላንድ ሰብሳቢ፤ ብሔረተኝነትና የዲሞክራሲ ፈተናዎች በኢትዮጵያ በሚል ርዕስ ዙሪያ፤ በተጨባጭ መረጃ አስደግፍው፣ እስከ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ጠላት የሆኑትን ኋላቀርነት፣ **ሠላም ማጣትና የመልካም አስተዳደር እጦት ወይም ጉድለት፦** መሆናቸውን በማስጤን፤ ብሎም የነዚህ ውጤት የሆነው <u>መሃይምነት፣ በሽታ፣ ድሕነትና ረሐብ</u> የመሳሰሉት፣ የአገራችን አሳፋሪና ዘግናኝ ችግሮች፦ ጎሳን፣ ቋንቋን፣ ሐይማኖትን፣ ፆታን፣ እድሜንና አካባቢን ሳይለይ፣ በጥቅሉ የአገሪቱን ዜጋ ለዘመናት ሲያጠቁት የቆዩ ቢሆንም፣ ዛሬ ከመቼውም በከፋ ሁኔታ ቅስሙን በመስበር፣ **እጅግ እያጠቁት** መሆናቸውን በማስገንዘብ፤ በተለይ ቀና አመለካከት ያላቸው ኢትዮጵያውያን፣ ችግሩን ለመታደግ፣ ከመቼውም በተለየ መልኩ በእርጋታና በጥንቃቄ ሊያጤኑት፣ ሊያስተውሉትና በቂ ግንዛቤ ሊቸሩት ይገባል በማለት ጉባኤውን በጥብቅ አሳሰበዋል።

በአገራችን ሕዝብ ላይ እነዚህ ከላይ የተገለፁት፣ ኋላ ቀር የአገዛዝ ሥርዓቶቻችንና የአገሪቱ የውስጥና የውጪ የታሪክ ጠላቶች ያስከተሉት የዘመናት ችግሮች መሆኑ ግልጽ ሁኖ እያለ፣ **በተለይ ፣ ቀለም ቀመስና ተምሬአለሁ የሚለው ኢትዮጵያዊ፣** በአብዛኛው ይህንን የጋራ የሆነውን ችግርና ጭቆና ተባበሮ በማስወገድ ፋንታ፣ ከዚህ ጋር ተዛማጂነት በሌለው መልኩ ሌላ የፈጠራ ታሪክ በመፍጠር፤ይህን **ሳይማር ያስተማረንን** ወገናችንን፤ **ድህነት፣ በሽታ፣ ረሃብ፣ ሠላም ማጣትና** ወከባ ቅስሙን የሠበሩት ሳያንሰው፤ ወደ ሌላ በቀላሉ ሊወጣው የማይችለው የተወሳሰበ ችግር ውስጥ በመክተት፤ ይሄው እንደምናየውና እንደምንሰማው፣ መፈጠሩን እስከሚጠላና እስከሚኮንን ድረስ ፍዳውን እንዲያይ እየተደረገ ነው።

ስለዚህ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ የምትሆን የህግ የበላይነት፣ የግለ ሰብና የቡድን ሰብዓዊ መብቶች የሚከበሩባት፣ የህዝብ ውክልና ያለውና ተጠሪነቱም ለመረጠው ሕዝብ ብሔራዊ ጥቅም የቆመ፣ ለሀገር አንድነትና ሉዓላዊነት የሚሠራና መልካም የአስተዳደር ሥርዓትን ለመፍጠር ወይም ለማምጣት፣ ዛሬ እየተደረገ ያለው ጥረት፣ ግቡን ቢመታ፣ ተጠቃሚው በእኩልነት ሁሉም የዛች አገር ዜጋ እንደሚሆን ከቶም አጠያያቂ አይሆንም። ይሁን እንጂ መፍትሄውና ቁምነገሩ ይህ ሆኖ ሳለ፣ የአገሪቱ ሕዝብ ያደረገውንና እያደረገ ያለውን የጋራ ተጋድሎ፣ ሆን ብለው፣ አዛብተው በማቅረብ፣ በተወሰነ ጎሳ የበላይነትነትና የበታችነት ክስተት እንደሆነ አፅንኦት በመስጠትና አንዱን ጎሳ ከሌላው ጎሳ ጋር በማጋጨት፣ የሥልጣን እድሜን ለማራዘም የሚደረግው ሙከራ፣ ፈፅሞ በሀገራችን ሰላም፣ መረጋጋትና ብልጽግናን ሊያመጣ አይችልም።

ይህንንም በማድረግ በስልጣን ላይ ለመቆየት ወይም በተመሳሳይ መልኩ ስልጣን ለመያዝ የሚደረገው ከንቱ ሙከራ፣ ዞሮ ዞሮ የመጨረሻ ውጤቱ፣ የቀለበት ውስጥ ሩጫ ወይም ከዚህም ካለፈ አጥፍቶ መጥፋት እንጂ፣ ሌላ ጠቃሚና ዘላቂ ውጤት እንደማይኖረው፣ ሁሉም የዚች አገር ዜጋ በጥንቃቄና በእርጋታ ሊያስተውለው ይገባል በማለት አሳስበዋል።

ይህን የአገሪቱን ሕዝብ ይሁንታ ያላገኘና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎትና ምኞት ጋር ሆድና ጀርባ የሆነውን፣ የወያኔ ኢህአዴግ የአፓርታይድ መርህ፣ እንደማይቀበለው ግንቦት 2005 ዓ ም፣ በተደረገው አገራዊ ምርጫ፣ በማያሻማ ሁኔታ ለዓለም ሕዝብ በተግባር አሳይቷል። ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትክክለኛ ፍላጎትና ቆራጥ ትግል ያስበረገገው፣ የወያኔ መንጋ፣ ከዛች እለት ጀምሮ የአገዛዝ እድሜውን ለማራዘም፣ በሁሉም አቅጣጫ የሕዝቡን የነፃነት ትግል ለማፈን በመፍጨርጨር ላይ ይገኛል።

ይህ በኢትዮጵያ ሕዝብና ይመሩኛል ብሎ በመረጣቸው ብርቅዬ ልጆቹ ላይ፣ በአምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ እየተፈፀመበት ያለውን፣ የሰብአዊ፣ የፍትሕና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን መገፈፍ አስመልክቶ የተደረገውን ማብራሪያና ገለፃ ላይ፣ ጉባኤው በጥልቀት ከተወያየ በኋላ፤ በሆላንድ ኗሪ የሆነው ኢትዮጵያዊ ሁሉ፣ በግልም ሆነ በጋራ ትግሉ ለሚጠይቀው፣ ዘርፈ ብዙና ሁሉን አቀፍ የተግባር ተሳትፎ፣ የበኩሉን ለማበርከት እንዲችል፣ ለመደራጀትና በጋራ ለመስራት ዝግጁነቱን እንዲያሳይ፣ የሚያሳስቡ መመሪያዎችንና ጥቆማዎችን ከሰጠ በኋል፣ የሚከተለውን የአቋም መግለጫ በማውጣት ስብሰባው ተጠናቋል።

1. በሀገራችን ኢትዮጵያ መልካም አስተዳደርን መሰረት ያደረገ የግልና የቡድን ሰብዓዊ መብቶች የሚከበሩበት፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ጎሳ፣ ቋንቋና ሐይማኖት ሳይወሰነው፣ በሰላም በሀገሩ ውስጥ ያለ ስጋት የሚንቀሣቀስበት፣ በሠላም ውሎ ወደ ቤቱ የሚገባበት፣ የሕግ የበላይነት የሚረጋገጥበት፣ ዜጎች በእኩልነት የሚታዩባት፣ የበለፀገች ኢትዮጵያን ለመገንባት፤ የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ በሠላማዊ መንገድ የሚያደርገውን ትግል ከልብ እንደግፋለን።

2. በውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ አካል የሆነውና በሆላንድ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ከጎናቸው በመቆም ሳያሰልስ በሚደረገው የዲፕሎማሲ፣ የገንዘብ፣ የእወቀት፣ የማቴርያልና የሞራል ድጋፉን፣ በለማቋረጥ እንዲያደርግ አጥብቀን እንጠይቃለን።

3 በሀገራችን ኢትዮጵያ ህገ መንግስታዊ መብታችውን በመጠቀም የሕዝብ ድምጽ ይከበር ዘንድ፣ ተቃውሞቸውን በማሰማታቸው ብቻ፣ በወያኔ/ ኢህአዴግ የጸጥታ ሀይሎች የሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብታቸው ተጥሶ እየደረሰባቸው ያለውን የህይወት፣ የአካልና የንብረት ውድመት፣ እስራት፣ ወከባና እንግልት አጥብቀን እናወገዛለን። የዓለም ህብረተሰብም ችግሩን በይበልጥ እንዲያውቀውና እንዲያወግዘው፣ በደሉን ያደረሱትም ለፍርድ እንዲቀርቡ፣ ኢትዮጵያውያን የህግ ባለሙያዎች መረጃዎችን በማሰባሰብና ጉዳዩን በማንቀሳቀስ ለውጤት እንዲያበቁት አቅማችን የሚችለውን ሁሉ ድጋፍ ለመስጠት ዝግጁነታችንን እንገልጻለን።

4. በእስር ላይ የሚገኙት የቅንጅት ከፍተኛ አመራር አካላት፣ ቀደም ብለው ለረዥም ጊዜ የታሠሩ የፖለቲካና የሕሊና እስረኞች፣ የሲቪክና የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች አመራር አባላት፣ የነጻው ፕሬስ አባላት ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ ተፈትተው፣ ያለአንዳች ወከባና እንግልት የተጣለባቸውን ሕዝባዊ አደራ፣ ሐላፊነትና ሙያዊ ግዴታ በብቃት እንዲወጡ እንጠይቃለን።

5. የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በተለይ የአሜሪካ መንግስት፣ የአውሮጳ ሕብረት፣ የዓለም ባንክና መሰል ድርጅቶች ሕዝባችንን አፍኖና ዲሞክራሲያዊ መብቱን ነፍጎ ፍጹም አምባገነናዊ የሆነ የአገዛዝ ሥርዓት እየመሰረተ ላለው ለወያኔ/ኢህአዴግ የሚሰጡትን የበጀት እርዳታም ሆነ ድጎማ አቁመው፣ ፍትህ ከተጠማው ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን እንዲቆሙ እንጠይቃለን።

6. የሐገራችንን ብሄራዊ ጥቅምና የሕዝባችንን ሁለንተናዊ ድል ለማቅረብ ከሚታገሉ ከሌሎች እውነተኛ ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር በሚያቀራርቡና የጋራ በሆኑ ብሔራዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ በቅርብ ተባብሮ ለመስራት ዝግጁነታችንን እናስታውቃለን።

7. ወያኔ/ኢህአዴግ ነጻውን ፕሬስ በማፈን፣ የሕዝብን የማወቅ መብት አፍኖ፣ በአገሪቱ አንጡራ ሃብት ፋይናንስ የሚደረገውን መገናኛ ብዙሐን፣ በራሱ ቁጥጥር ስር ብቻ በማድረግ አገር አፍራሽ ለሆነው ፕሮፓጋንዳው መገልገያ፣ ማድረጉን አጥብቀን እያወገዝን፤ መገናኛ ብዙሐን ለሁሉም ያለምንም ገደብ በእኩልነት እንዲያገለግልና አላግባብ የታሰሩት የነጻው ፕሬስ አባላት ከእስር ተፈትተው ለዲሞክራሲያዊ ሥራዓት ግንባታው የተለመደውን ሙያዊ አገልግሎታቸውን ለሕዝቡ እንዲሰጡ በጥብቅ እናሳስባለን።

8. በሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው የቅንጅት አመራር በእስር ላይ እያለ፣ ሌላ ተለጣፊ ድርጅት ለማቋቋም የሚደረገውን የክህደት ሴራና ማጭበርበር እጅግ አጥብቀን እናወግዛለን።

9. የተቋቋመው **አውሮጳ አቀፍ የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ፣** በአፋጣኝ ተጠናክሮ፣ ከሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር **የሠከነና ማዕከላዊ** የሆነ እቅድ በማውጣት፣ ለተግባራዊ አፈጻጸሙም ዝርዝር መመሪያ እንዲወጣና ትግሉ የሚጠይቀውን፣ የየበኩላችንን የሥራ ድርሻ ለማበርከት እንድንችል አስፈላጊው ጥረት ሁሉ እንዲደርግ ከልብ እያሳሰብን፣ እቅዱንም ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁነታችንን እናስታውቃለን።

Contact us: Address P. o box 25763, 2502 HT The Hague, Phone No. +03120-6916923, +0 3170-4451682, Email kinijit.sch@gmail.com

10. የአዲስ አበባ ሕዝብ በመረጠው ፓርቲ እንዳይተዳደርና የመረጣቸውን እንደራሴዎቹንና ከንቲባውን ዶ/ር ብርሀኑ ነጋን ጨምሮ በፈጠራ ወንጀል ለእስር ዳርጎ ባልመረጣቸው ወይም በተለጣፊዎች ለማስተዳደር የሚድረገው ሕዝብን የናቀ ውንብድናና ይህ ነገን የማያልፍ ከንቱ ሩጫ እንዲቆም አብጥቀን እንጠይቃለን።

11. በሆላንድ ውስጥ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ግንዛቤውን ከፍ በማድረግ በመረጠው የትግል ስልት ተሰልፎ፣ በአገር ውስጥ የሚኖረው ወገኑ ከገዛ አብራኩ በወጡና ማስተዋል በተሳናቸው ልጆቹ ከደረሰበት ችግር ለመላቀቅና ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ እየከፈለ ላለው ከፍተኛ መስዋዕትነት፣ ትግሉ ግቡን እስከሚመታ ድረስ፣ ከወገኑ ጎን ተሰልፎ የማያቋርጥ እገዛ በማድረግ፣ የሚጠበቅበትን የዜግነት ድርሻውን በትጋት እንዲወጣ ጥሪ እያደረግን ፥የመተባበር ሃይላችን እንዳይጠናከር ሁልጊዜ ፀር ከሆነው፣ በተለይም ከአሉባልታና ከፋፋይ ከሆኑ አፍራሽ ተግባራት ተቆጥበን ብሔራዊ ትግሉን ለማጎልበት ጥረት ለማድረግ ቃል በመግባት ጠቅላላ ስብሰባው ተጠናቋል።

***የቅንጅት ሕልውና መሠረቱ ሕዝባዊ ድጋፉ ነው !!!***

**አፕሪል 08 ቀን 2006**

**አምስተርዳም**

Contact us: Address P. o box 25763, 2502 HT The Hague, Phone No.  +03120-6916923, +0 3170-4451682, Email kinijit.sch@gmail.com